

# ወንጌላዊው ፊሊጶስ

- አስጢፋኖስ ተወግሮ ከሞተ በኋላ በኢየሩሳሌም ውስጥ በሚኖሩ ክርስቲያኖች ላይ በጣም ትልቅ ስደት ተነሳባቸው። ሳውል ከቤት ወደቤት እየተዘዋወረ ሰዎችን ከቤታቸው ጎትቶ እያስወጣ ወደ እስር ቤት ያስገባ ነበር።

- ብዙ ክርስቲያኖችም እንዳይሞቱ በመፍራት ከኢየሩሳሌም ሸሽተው ወደሌሎች ስፍራዎች ተሰደዱ። በተለያዩ ምክንያቶች ሐዋርያት የእግዚአብሔር ጥበቃ ስለበዘላቸው ከኢየሩሳሌም አልወጡም፣ አልታሰሩምም ነበር።

- በዚህ ታሪክ ላይ የምናየው ፊሊጶስ ሐዋርያው ፊሊጶስ አይደለም። በኢየሩሳሌም የነበሩትን መበለቶች እንዲንከባከብ ከተመረጡት ሰባት ሰዎች መካከል አንደኛው ነበር። እርሱም እንደሌሎቹ እንደተሰደዱት ክርስቲያኖች ወደሰማርያ አካባቢ ነበር የተሰደደው።

- አንድ ቀን የጌታ መልአክ ተገልጦለት ከኢየሩሳሌም ወደጋዛ በሚወስደውና በሜዲቴራኒያን ባህር አጠገብ ወዳለ ጎዳና በደቡብ አቅጣጫ እንዲጓዝ አዘዘው። በዚያም ከኢትዮጵያ የመጣ አንድ ሰው ያገኛል። ሰውዬው በሰረገላ ይጓዝ ነበር። ይህ ሰው በአገሩ መንግስት ውስጥ ከፍተኛ ስልጣን የነበረው ሰው ነበር። ህንደኬ የተባለችው የአገሪቱ ንግስት ይህን ሰው በወርቅ በብርና በሌላው የመንግስቷ ሀብት ላይ ሾማው ነበር።

❋ በእግዚአብሔር የሚያምን ሰው ስለነበርም እግዚአብሔርን ለማምለክ ወደ ኢየሩሳሌም ተጓዘ። ይህ ሰው አይሁዳዊ አልነበረም። ሆኖም የአይሁድን የኃይማኖት ትምህርት ከተማረና እንደ ጥምቀት የመሳሰሉ አንዳንድ ኃይማኖታዊ ስርዓቶችን ከፈፀመ በኋላ ወደይሁዲነት የተለወጠ ሰው እንደነበር ይገመታል። እንደዚህ አይነት ሰዎች የአይሁዳውያንን ኃይማኖት ከተቀበሉ በኋላ አይሁዳዊ ስም ይወጣላቸው ነበር። ፊሊጶስም ይህ ኢትዮጵያዊ ይጓዝበት ወደነበረው ሰረገላ ተጠጋ። ኢትዮጵያዊውም ከነቢዩ ከኢያሳያስ መፅሐፍ እያነበበ አየው።

❋ "ለመሆኑ የምታነበውን ትረዳዋለህ?" ሲል ጠየቀው። ኢትዮጵያዊውም የሚያስረዳኝ ሰው እፈልጋለሁ ካለው በኋላ ፊሊጶስን በሰረገላው ውስጥ እንዲቀመጥ ጋበዘው። ከዚያም ጉዟቸውን ቀጠሉ። አሁን ኢትዮጵያዊው የሚያነበው የመፅሐፍ ቅዱስ የተፃፈው ከ500 አመታት በፊት የተፃፈ ነበር። ክፍሉ የሚያወራው ስለ አንድ ያለአግባብ ምርመራ ስለሚካሄድበትና ስለሚፈረድበት ሰው ነው። ይህም ሰው በፍርድ ሂደቱ ወቅት ራሱን ለመከላከል ምንም አይነት ሙከራ አያደርግም ነበር።

❋ ኢትዮጵያዊውም ፊሊጶስን፣ "ነቢዩ የፃፈው ስለራሱ ነው ወይንስ ስለሌላ ሰው?" በማለት ጠየቀው።

❋ ፊሊጶስም ከዚህ የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል በመጀመር ስለኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት መልካም ዜና ነገረው። ይህም መልካም ዜና ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት ወደምድር እንደመጣ፣ እንዴት እንደተገደለና እግዚአብሔርም እንዴት ከሞት እንዳስነሳው የሚገልጥ ዜና ነበር። ከዚህ ጋር አያይዞም ስለ ጥምቀት እንዳስተማረው እርግጠኞች መሆን እንችላለን። ምክንያቱም ውኃ ወዳለበት አካባቢ እንደደረሱ ኢትዮጵያዊው ፊሊጶስን፣ "በውኃ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ነገር አለ ወይ?" ብሎ ሲጠይቀው እናያለንና። ከዚያም ኢትዮጵያዊው ሰረገላው እንዲቆም ያዛል። ፊሊጶስም፣ "በፍፁም ልብህ ብታምን ልትጠመቅ ትችላለህ፣" አለው።

❋ ኢትዮጵያዊውም፣ "ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ፣" አለ።

❋ ሁለቱም ወደ ውኃ ወዳለበት ወንዝ ወረዱ። ፊሊጶስም ሰውዬውን አጠመቀው። መጠመቅ የሚለው ቃል በውሃ ውስጥ ሙሉ በሙሉ መዘፈቅ ወይንም መጥለቅ ማለት ነው። ልክ እንደመቀበር ማለት ነው። ይህም የሚጠመቀው ሰው ልክ እንደሞተና እንደተቀበረ፣ እንዲሁም እንደገና ከሞት እንደተነሳ የሚያሳይ ስርዓት ነው። በዚህ ስር□ት ውስጥ የሚያልፍ ሰው አዲስ ሰው እንደሆነ ይቆጠራል።

❋ የእግዚአብሔር መንፈስ ፊሊጶስን ወሰደው። ወደሌላ ስፍራ በአስደናቂ ፍጥነት ይወሰድ ወይንም ወደሚቀጥለው ስፍራ ሄዶ እንዲሰብክ መታዘዙን ግን በእርግጠኝነት መናገር አይቻልም። ለማንኛውም ኢትዮጵያዊው ፊሊጶስን ዳግመኛ አላየውም።

❋ በሰረገላ የቀረውን ኢትዮጵያዊ በተመለከተ ግን ኢየሱስን በማግኘቱ በጣም ደስተኛ እንደነበርና ከእግዚብሔር ልጅና ከእግዚአብሔር አብ ጋር አስደናቂ ግንኙነት ስለመሰረተ ደስ ብሎት ጉዞውን እንደቀጠለ እናነባለን።

*ይህ የፊሊጶስና የኢትዮጵያዊው ታሪክ የሚገኘው በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 8፡ 26 – 40 ውስጥ ነው።*

http://gardenofpraise.com